https://t.me/ethiopianlegalbrief

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

**የመ.ቁ.223966**

**ጥቅምት 01/2015 ዓ.ም**

**ዳኞች፡ እትመት አሰፋ**

**ፀሐይ መንክር**

**ኑረዲን ከድር**

**መላኩ ካሳዬ**

**እስቲበል አንዱዓለም**

**አመልካች፡** **የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ** } **የቀረበ የለም**

**ተጠሪ፡** **ስንታየሁ አበበ**

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

በዚህ መዝገብ ላይ የቀረበው ጉዳይ ከባድ የሰው ግድያ ወንጀልን የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የቀረበውም አመልካች በስር ፍርድ ቤት በአሁን ተጠሪ ላይ ያቀረበው ደጋጋሚ የወንጀል ሪኮርድ በቅጣት ማክበጃነት ያልተያዘበትን ህጋዊ ምክንያት መርምሮ ለመወሰን ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው የአሁን አመልካች ግንቦት 06/2011 ዓ.ም ፅፎ በአሁን ተጠሪ ላይ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀረበው የወንጀል ክስ ነው፡፡ የክሱም ጭብጥ ተጠሪ የወንጀል ህግ አንቀፅ 539(1(ሀ)) ድንጋጌን በመተላለፍ ሰው ለመግደል አስቦ በክሱ ዝርዝር በተገለፀው ቀን፣ ቦታ እና ሰዓት ሲዝናናበት ከነበረው ሆቴል ውስጥ "ውጣ! አልወጣም!" በሚል በተፈጠረ ፀብ አደገኛነቱን እና ጨካኝነቱን በሚያሳይ ሁኔታ በያዘው ቢላዋ ሟች አቶ አለማየሁ ግርማ የተባለውን ሆዱ እና ደረቱ ላይ ደጋግሞ በመውጋት የገደለው በመሆኑ ከባድ የሰው መግደል ወንጀል ፈፅሟል የሚል ነው፡፡

የአሁን ተጠሪ ለዚሁ ክስ በሰጠው መልስ ድርጊቱን በመጠጥ መንፈስ የፈፀመ መሆኑን ገልፆ "ጥፋተኛ አይደለሁም!" ሲል ክዶ ተከራክሯል፡፡ በዚሁ መሰረት የዐቃቤ ህግ ማስረጃ ተሰምቶ ተጠሪ ክስ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በቀረበበት አንቀፅ ስር እንዲከላከል ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡ የተጠሪ መከላከያ ምስክሮች ከተሰሙ በኋላም ተጠሪ ክስ እና ማስረጃውን አላስተባበለም በሚል በተከሰሰበት አንቀፅ ስር ጥፋተኛ ተብሏል፡፡ ግራ ቀኙ ስለቅጣቱ አወሳሰን ያላቸውን አስተያየት እንዲያቀርቡ በታዘዙት መሰረት የአሁን አመልካች ተጠሪ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/160130 ላይ የካቲት 02/2008 ዓ.ም በውንብድና ወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ በ1 ዓመት ከ8 ወር ፅኑ እስራት የተቀጣ መሆኑን ገልፆ በደጋጋሚ ወንጀለኛነት ቅጣቱ ከብዶ እንዲወሰን ጠይቋል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ የቅጣት ማቅለያ ናቸው ያላቸውን አራት ምክንያቶች አቅርቧል፡፡

ጉዳዩን የቀረበለት ፍርድ ቤትም የጥፋተኝነት ፍርድ ለተሰጠበት ወንጀል በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 02/2006 ደረጃ እና እርከን የወጣለት መሆኑን ጠቅሶ በደረጃ 1 እርከን 38 ስር የእድሜ ልክ ፅኑ እስራትን በመነሻ ቅጣትነት ይዟል፡፡ ከዚህ በኋላ በመነሻ ቅጣትነት የተያዘው የእድሜ ልክ እስራት የፅኑ እስራት ጣሪያ በመሆኑ ዐቃቤ ህግ ባቀረበው ቅጣት ማክበጃ ምክንያት ቅጣቱ ከዚህ በላይ ሊከብድ አይችልም በሚል የቅጣት ማክበጃ ምክንያቱን ሳይዝ አልፏል፡፡ ከቅጣት ማቅለያ አንፃር ተጠሪ ካቀረባቸው አራት ምክንያቶች ውስጥ ሁለቱን በመቀበል መነሻ እርከኑን ወደ እርከን 36 ዝቅ አድርጎ ተጠሪ በ18 ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጣ በአብላጫ ድምጽ ወስኗል፡፡ የልዩነት ሀሳብ የያዙት ዳኛ ደግሞ ተጠሪ ደጋጋሚ ወንጀለኛ ስለመሆኑ በማስረጃ ተረጋግጦ እያለ ዐቃቤ ህግ ያቀረበው የቅጣት ማክበጃ ምክንያት መታፉ አግባብ አይደለም በማለት ከቅጣቱ አወሳሰን አንፃር የተለየ አቋም ይዘዋል፡፡

አመልካች የቅጣት ማክበጃው ሳይያዝ መታለፉን በመቃወም ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ ይግባኙን በወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥ 195(1) መሰረት ዘግቷል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ነው፡፡ አመልካች መጋቢት 21/2014 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ በቅጣት አወሳሰን አንፃር በስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ላይ ተፈጽሟል ያለውን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሶ በዚህ ችሎት እንዲታረምለት ጠይቋል፡፡ የቀረበው ሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ከላይ በዚህ ፍርድ መግቢያ ላይ የተጠቀሰውን ነጥብ ግራ ቀኙ በተገኙበት አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ ታዝዞ ግራ ቀኙ በፅሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና መሰረታዊ የክርክሩ ይዘት አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራ ቀኙ ክርክር፣ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

አመልካች በተጠሪ ላይ የወንጀል ቅጣት ማክበጃ ያቀረበው ደጋጋሚ ወንጀለኛ ነው በሚል ነው፡፡ አንድ ወንጀል አድራጊ ደጋጋሚ ወንጀለኛ ነው ተብሎ ቅጣት የሚከብድብት ቀደም ሲል የተወሰነበትን የእስራት ቅጣት በሙሉ ወይም በከፊል ከፈፀመበት ወይም ቅጣቱ በይቅርታ ከቀረለት ቀን ጀምሮ በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ መነሻ ቅጣቱ ስድስት ወር የሆነ ቀላል እስራት ማስቀጣት የሚችል አዲስ ወንጀል አስቦ ስለመፈፀሙ ሲረጋገጥ እንደሆነ ከወንጀል ህግ አንቀፅ 67 እና 188 ድንጋጌች ጣምራ ንባብ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከወንጀል ቅጣት አወሳሰን ጋር ተያይዞ ማክበጃ እና ማቅለያ ምክንያቶች የሚታዩትም በቅድሚያ የቅጣት አስተያየቶቹ ከግንዛቤ ሳይገቡ መነሻ ቅጣት ከተለየ በኋላ ስለመሆኑ የወንጀል ህግ አንቀጽ 88(2) ይደነግጋል፡፡ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 02/2006 መሰረት ደረጃ እና እርከን የወጣላቸው የወንጀል ጉዳዮችን በተመለከተ ደግሞ በቅድሚያ የወንጀሉ ደረጃ እና እርከን ከተለየ በኋላ ስለመሆኑ የመመሪያ አንቀፅ 26(1) ይደነግጋል፡፡ በመመሪያው መሰረት በቅጣት ማክበጃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እና ማቃለያ ምክንያት የሚከብደውም ሆነ የሚቀንሰው የቅጣት እርከኑ እንደሆነ በዚሁ ድንጋጌ ስር ተመልክቷል፡፡ በሌላ በኩል ስለ ተደራራቢ ወንጀሎች የተመለከው የቅጣት አሰላል እንደተጠበቀ ሆኖ የቅጣት ማክበጃ እና ማቅለያ ምክንያት በተገኘ ጊዜ በመነሻ እርከኑ በተመለከተው ፍቅደ ስልጣን ውስጥ መነሻ ቅጣትን መያዝ አስፈላጊ እንዳልሆነ በመመሪያው አንቀፅ 26(1(መ)) ስር ተመልክቷል፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ ተጠሪ ጥፋተኛ ለተባለበት ወንጀል በቅጣት አወሳሳን መመሪያ ቁጥር 02/2006 መሰረት የወንጀሉ ደረጃ 01፣ የቅጣት እርከን 38 መሆኑ ተለይቷል፡፡ በዚህ እርከን ስር ያለው ቅጣት ከእድሜ ልክ እስራት እስከ ሞት በሚደርስ ቅጣት የሚያስቀጣ ቢሆንም በግራ ቀኙ የቀረበ የቅጣት አስተያየት ያለ በመሆኑ በፍቅደ ስልጣኑ ውስጥ መነሻ ቅጣትን መያዝ አስፈላጊ አይደለም፡፡ ከዚህ ይልቅ የሚጠበቀው የቀረቡትን የቅጣት ሀሳቦች መነሻ በማድረግ እንደሁኔታው እርከኑን ከፍ ወይም ዝቅ ማድረግ ነው፡፡ በዚሁ አግባብ ተጠሪ የደጋጋሚ ወንጀለኝነት መመዘኛን የሚያሟላ ስለመሆኑ የስር ፍርድ ቤት የተቀበለው ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ ችሎት እይታም ቢሆን ተጠሪ በ2008 ዓ.ም በፅኑ እስራት ቅጣት እንዲቀጣ ተወስኖበት አሁን ጥፋተኛ የተባለበትን ወንጀል በ2011 ዓም ውስጥ በአውቆ አጥፊነት የፈፀመ በመሆኑ መመዘኛውን የሚያሟላ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም በእርከኑ ፍቅደ ስልጣን ውስጥ መነሻ ቅጣትን መያዝ ሳያስፈልግ የቅጣት እርከኑ ወደ እርከን 39 ከፍ ሊደረግ የሚገባው ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት በዚህ መልኩ ቅጣቱን ማስላት ሲገባው ተገቢ ባልሆነ መንገድ በመነሻ ፍቅደ ስልጣኑ ውስጥ መነሻ ቅጣት በመያዝ ማክበጃ ምክንያቱን ሳይቀበል መቅረቱ የተሻሻለውን የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 02/2006 አንቀፅ 26(1(መ)) ድንጋጌን ያልተከተለ በመሆኑ ሊታረም የሚገባው መሰረታዊ የህግ ስህተት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመሆኑም የቅጣት እርከኑ ወደ እርከን 39 ከፍ ተደርጓል፡፡ በስር ፍርድ ቤት ተቀባይነት ያገኙ ሁለት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ያሉ በመሆኑ ከብዶ የተያዘው የቅጣት እርከን ወደ እርከን 37 ዝቅ ብሏል፡፡ በዚህ እርከን ስር ያለው ቅጣት ከ20 ዓመት እስከ 25 ዓመት ጽኑ እስራት ነው፡፡ ስለሆነም በተቀመጠው ፍቅደ ስልጣን ውስጥ ተጠሪ በ20(ሃያ) ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ተወስኗል፡፡

## ውሳኔ

1. በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ/238255 ላይ ጥቅምት 23/2014 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በወ/መ/ቁ/217084 ላይ ጥር 25/2014 ዐ.ም. በተሰጠ ትዕዛዝ የፀናው የቅጣት ውሳኔ በወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 195(2(ለ(2))) መሰረት ተሻሽሎ ተጠሪ በዚህ ጉዳይ እጁ ከተያዘበት ቀን ጀምሮ በሚታሰብ በ20(ሃያ) ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ተወስኗል፡፡

2. በተሻሻለው የቅጣት ውሳኔ መሰረት ተከታትሎ እንዲያስፈፅም ተጠሪ ለሚገኝበት ማረሚያ ቤት ይፃፍ፡፡

3. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም